# አባይ ፤ በአባይ ፤ ተታለህ

አገሬ ከስዊድን ሰኔ 2011

አወዛጋቢው የአባይ ግድብ በኢትዮጵያዊው ላይ ስነ ልቦናዊ ጫና ማሳደሩ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት አንደኛ ኢትዮጵያዊ በዛች ምድር ተፈጥሮ ተመልሶ የዚህን አለም ሩጫ ጨርሶ ወደ ከርሰ መቃብር እስከሚገባ ድረስ የሚመኘው አባይ ፊቱን ወደ እናት አገሩ መልሶ ሲፈስ ማየት መሆኑ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ይህ የኢትዩጵያ ህዝብ ተስፋና ናፍቆት የሆነው ወንዝ መገደብን በተመለከተ ድንገት ከፈላጭ ቆራጩ የወያኔ አገዛዝ የተከሰተው ትዕይንት ይሆናል።

አባይ መገደቡ ባልከፋ፤ አሳዛኙ ሁኔታ ግን የኢዮጵያን ጥቅም በማስጠበቅ የማይታወቀው ፈላጭ ቆራጩ የወያኔ አገዛዝ በኑሮ ውድነት የሚጎሳቆለውን፤ በቀን ሶስት ጊዜ መብላት ካቆመ አመታት ያስቆጠረውን ህዝብ ለግድቡ የወር ደመወዝህን አምጣ ብሎ ጫና መጣሉ ሲሆን፤ ስንኙ የተቋጠረው ምርጫ ቢሱ የኢትዮጵያ ህዝብ በወደቀበት ጫናና ግድቡ ተግባር ላይ መዋሉ አስተማማኝ ባልሆነበት ነገር ላይ ተመርኩዞ በውስጡ የፈጠረውን ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ለማንፀባረቅ ነው።

የኛ ያልንህ ፤ አባይ ትልቁ
የወንዝ የበላይ ፤ ተጓዥ በሩቁ
ወደር የለህ ፤ በርዝመት
ሄደህ ሄደህ ፤ አትታክት
የወንዝ አውራ ፤ ታላቅ መሪ
ተላላ ነህ ፤ ነዉር ሰሪ
በስደትህ ፤ አጋፋሪ
ብለህ ብለህ ፤ ብለህ አሁን
የአገርህ ልጅ ፤ ኩራትህን
በራብ ጨርሰን ፤ እስኪ ይሁን !
<u>አባይ</u> ፤ በአባይ ፤ ተታለህ
እኛን ለአባይ ፤ አመቸቸህ !
ተመልሰህ ልትገባ ፤ ቤትህ?

ፊትህን ልታዞር ፣ ወደ እናትህ?

አስደሰትክ ፣ ስንቱን በተስፋ

ስንቱስ ፣ በጦስህ ጠፋ

ለስንቅህ ፣ ባለው ገፈፋ

ያገሬ ልጅ ፣ ግዙፋ አባይ

የኛ ተስፋ ፣ የባእድ ሲሳይ

መጥተህ ላትመጣ ፣ ሆኖ ላይሆን

ደግሞ ያሁኑ ፣ ለምን ይሆን?

እንዲያው አልኩህ እንጅ ፣ ኩራቴ

የአገር ልጅ ፣ ብዬ ሞኝነቴ

ምን አድርገሀል ፣ ለእናቴ

እስኪ ንገረኝ ፣ አባይ በሞቴ?

አንተ የጎረቤት ፣ ቤት አሟቂ

የባዕድ ከተማ ፣ አድማቂ

አባይ የበርሀ ፣ አገሮች አባት

የምድረ ግብፅ ፣ ድምቀት ውበት

መተዳደሪያ ፣ አለኝታቸዉ

የኢኮኖሚ ፣ አውታራቸው

አባይ ፣ ባለግርማ ሞገሱ

የአፈር ሌባው ፣ ድፍርሱ

ድንቅ ተባልክ ፣ ተሞካሸህ

የሰው አገር ፣ ሲሳይ ሆነህ

ግብዙ አባይ ፣ ተላለው

የአለምን ቀልብ ፣ ያማለልከው

በሰው አገር ፣ የነገስከው

አባይ ተላላ ፣ በአባይ ተታላይ

ጦስህ ለእኔ ተረፈ ፣ ደግሞ መከራየን ላይ ።

አንተ መጥተህ ፣ ላትመጣ

ዉሎ አዳሬ ፣ ቅጡን አጣ

ከርታታው ፣ ያገሬ ልጅ አባይ

አባይ አገኘህ ፣ አታላይ

የኔን ልንገርህ ፣ ቀርቤ

ከነዘር ማንዘሬ ፣ ተርቤ

EthioLion.Com

ስንቅህን ሰነቅኩ ፣ ለአንተ መምጫ
ሳለምንበት ፣ ባጣ ምርጫ
እንዳለምን ፣ ውነት አልባ
እንዳልጨክን ፣ ሆዴ ባባ
ስተርትብህ ፣ ጥልቅ እያልኩ
ስቀኝ ሳዜም ፣ እንዳልኖርኩ
ዛሬ በስምህ ፣ ተራብኩ
አባይ ፣ የባዶ ኩራቴ
የሚቀመስ ፣ ጠፋ እቤቴ
ተጣጠፊልህ ፣ አንጀቴ
ቁርጥ ነው ፣ ነገ መሞቴ
ግን አባይ... መምጣትህ ፣ ዉነት ካልሆነ
የባዶው ቃል ፣ ካልታመነ
አባይ ፣ አባዩ ፣ ተንከራተት
እንደወጣህ ፣ ቅር ባለበት
በየ በረሀዉ ፣ ተኀተት ።

EthioLion.Com